# «አንድነት የሚታገለዉ ለኢሕአዴግ የምርጫ አጃቢነት ሚና ለመጫወት አይደለም» - አንድነት

የካቲት 19 ቀን 2001
ልዩ ዘገባ - ከአወደ ኢትዮጵያ

የአለም አቀፍና የአገር ዉስጥ ጋዜጠኞች በተገኙበት የአንድነት ፓርቲ ሰፋ ያለ ጋዜጣዊ መግለጫ ዛሬ የካቲት 19 ቀን 2001 ዓ.ም እንደሰጠ ለማወቅ ችለናል። በዚህ ጋዜጣዊ መግለጫ፣ በገዢዉ ፓርቲ በማእከልና በክልል ደረጃ ከፍተኛ ወከባና ተጽእኖ እየደረሰበት እንደሆነ የአንድነት ፓርቲ መረጃ ላይ የተመሰረተ ገለጻ አቅርቧል።

የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት የዜጎችን የመደራጀትና ሃሳባቸዉን በነጻ የመግለጽ መብትን እንደሚደነግግ፣ የመንግስት አካላትም የአገሪቱ የበላይ ሕግ የሆነዉን ሕገ መንግስቱን የማስከበር ግዴታ እንደነበረባቸዉ በማስታወስ፣ ከድርጅቱ ሊቀመንበር ጀምሮ እስከ ክልል አባላት ድርስ በተለያየ መስክ እየደረሰ ያለዉ ሕገ ወጥ ተግባራት እጅግ በጣም አሳሳቢና አገሪቷን ወደ ከፋ ደረጃ ሊወስድ እንደሚችል የፓርቲዉ አመራር አባላት አስረድተዋል።

በማእከል ደረጃ በገዢዉ ፓርቲ እየተወሰደ ያለዉን ጸረ-ዲሞክራሲያዊ አሰራር ለማሳየት እንደምሳሌነት ከተጠቀሱት ዉስጥ በዋናነት የድርጅቱ ሊቀመንበር ክብርት ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ላይ የተወሰደዉ ሕገ ወጥና ጭካኔ የተሞላበት ድርጊት ነበር።

ወ/ት ብርቱካን ለሁለት ወራት ሕገ መንግስታዊ መብታቸዉ ተነፍጎ፣ ጉዳያቸዉን ፍርድ ቤት እንዳያቀርቡ ታግደዉና በጨለማ ቤት ዉስጥ እንዲቀመጡ መደረጉ እጅግ እንዳስቆጣቸዉ የገለጹት የአንድነት መሪዎች፣ ገዢዉ ፓርቲ ሕገ መንግስቱን ከመናድ ተቆጥቦ፣ እራሱን ለሕግ እንዲያስገዛና የፓርቲዉን ቁራጥ ሊቀመንብር በአስቸኳይ እንዲፈታ አስገንዝበዋል።

ሌላዉ በማዕከል ለሚቀርበዉ ጸረ-ዲሞርካሲያዉ የገዢዉ ፓርቲ ተግባራት እንደምሳሌ የተጠቀሰዉ በአዲስ አበባ ሊደረግ የታሰበዉ የአንድነት ወጣቶች የኪነጥበብ ምሽትን የተመለከተ ነዉ። የአፍሪካ ሕብረት ስብሰባ ስለነበረ በወጣቶች ሊደረግ የታሰበዉ ዝግጅት መተለለፉን ያስታወሱት የአንድነት አመራር አባላት፣ አሁን እንደገና ያንን ዝግጅት ለማድረግ ጠይቀዉ በመንግስት አካላት ሕገ መንግስታዊ መብታቸዉን ተረግጦ እንደተከለከሉ ገልጸዋል።

«ማን ያዉራ የነበረ። ማን ያርዳ የቀበረ» እንደተባለዉ በክልል ደረጃ እየደረሰ ያለዉን ወከባ በተመለከተ ከአራት ክልሎች የመጡ የአንድነት የክልል አመራራ አባላት እርሳቸዉ በጋዜጣዊ መግለጫዉ ወቅት ተገኝተዉ ማብራሪያ በመስጠት

ገዢው ፓርቲ ምን ያህል የአንድነት ፓርቲ ላይ ጫና እያደረገ እንዳለ አጋልጠዋል።

በምስራቅ ጎጃም (ደብረ ማርቆስ አካባቢ) የዞኑ ሥራ አስፈጻሚ አባል አቶ ሉልሰገድ ፣ ፓርቲዉ ካለዉ የገንዘብ እጥረት የተነሳ ሕዝቡ እራሱ ከፍቶ የሚያንቀሳቅሳቸዉ አምስት የአንድነት ፓርቲ ጽ/ቤቶች ( ራስ አገዝ ቢሮውች) በክልሉ ባላሥልጣናት በጉልበት እንዲዘጉ የተደረገ እንደሆነና የአንድነት አባላት ፓርቲያቸዉን ከመደገፍ እንዲቆጠቡ፣ እንዲሁም እያደረጉት ካለ ዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ ቢታቀቡ እንደሚቻል በመናገር ከፍተኛ ማስፈራራትና ዛቻ እየደረሰባቸዉ እንደሆነ አስረድተዋል።

በኦሮሞያ በኢሊባቡር መቱ  ነዋሪ የሆኑ አቶ ዳንዔል ወልደገብሬል የሚባሉ የአንድነት አስተባባሪ በተራቸዉ፣ ከዚህ በፊት ለ27 ቀናት ፣  አሁን በቅርቡ ደግሞ ለሳምንት ታስረዉ እንደተፈቱ አስረድተዉ ፣በክልሉ ባለሥልጣናት እየደረሰ ያለዉ ግፍ እየጠነከረ መምጣቱን ገልጸዋል። «እኛ የመጣነዉ በጦር መሳሪያ ተዋግተን ነዉ። ከፈለጋቹህ እናንተም እንደኛዉ አድርጉ። እኛ በሞትንበት እናንተ በቀላሉ በምርጫ  ሥልጣን  መቼም አትይዙም» እያሉ  ለዲሞክራሲና ለሕግ የበላይነት ያላቸዉን ንቀት የክልሉ ባለሥልጣናት እየገለጹ እንደሆነ የተናገሩት አቶ ዳንዔል፣ ሃያ የሚሆኑ የአንድነት ፓርቲ አባላትን ስም ዝርዝር የያዘን ወረቀት በመቱና አካባቢዉ ለሚኖረዉ ሕዝብ በማሰራጨት «እነዚህ ሰዎችን እንዳትቀበሉ። እንዳትሰሚቸው» የሚል ማሳፈራራትም በሕዝቡ ላይ እየደረሰ እንደሆነና የገዚዉ ፓርቲ የክልል አስተዳዳሪዎች ሕገ ወጥ ተግባራት በመፈጸም ላይ እንዳሉ አጋልጠዋል።

በጎፋ ሳወላ እንደዚሁ ለበርካታ ቀናት ታሰረዉ የነበሩና ከተፈቱ ስድት ቀናቸዉ የሆነ፣ እርሳቸዉም አቶ ዳንዕል የሚባሉ የዞኑ የአንድነት ሃላፊ፣ በአካባቢያቸዉ እየተደረገ ያለዉን ግፍና የፖለቲካ ተጽእኖ በሰፊዉ ያብራሩ ሲሆን፣ ያለ ጥፋታቸዉ ከፍርድ ቤት ወረቀት ሳይመጣ በግፍ እንደታሰሩ የገለጹት አቶ ዳንዔል፣ የክልሉ የአንድነት ፓርቲ ጽ/ቤት ለፍርድ ቤት ክስ አቀርቦ በፍርድ ሂደቱ ጊዜ አሳሪ ፖሊሶቹ ስላልተገኑ ሊፈቱ እንደቻሉም አስረድተዋል።

በወዲቲ ወላይታ ዞን ተወካይ ባደረጉት ገለጻ የአንድነት አባላት አንድ ጽ/ቤት ተከራይተዉ ይንቀሳቀሱ በነበረበት ወቅት፣  የክልሉ ባለሥልጣናት ከቢሮ አስወጥተዉ ቤቱን በሌላ ቁልፍ ቆልፈዉባቸዉ እንደሄዱ ያስረዱ ሲሆን አባላቱ ግን ተስፋ ሳይቆርጡ እንደገና ሌላ ጽ/ቤት እንደነበረ ገልጸዋል። ነገር ግን ሁለተኛ ቢሮዋቸዉ ዉስጥ  ሳሉ ወደ 16 የሚሆኑ የገዢዉ ፓርቲ የክልሉ ባለሥልጣናት በጉልበት የኢትዮጵያን ባንዲራ አወርደዉ፣ ሰንደቁንም ነቅለዉ ለሁለተኛ ጊዜ ቢሮዋቸዉን ሊዘጉት እንደቻሉ የሳወላ የአንድነት ተወካይ ይፋ አደርገዋል።

ይህ በማእከልም ሆነ በክልል ደረጃ በአንድነት ፓርቲ እየደረሰ ያለዉ ጫናና ወከባ እጅግ እንዳሳሰባቸዉ የገለጹት የአንድነት አመራር አባላት ገዢዉ ፓርቲ ሕዝቡን ተስፋ አስቆርጦ፣ ራስ ምታት የሆነበትን የሰላማዊ ትግልን ለማጥፋት እየሞከረ እንደሆነ፣ ድርጅቱ ግን በሕዝብ ከመተማመንና ከሰላምዊ ትግል ዉይጭ ሌላ

አማራጭ ስለሌለዉ፣ በከተማ፣ በገጠር፣ በአገር ዉስጥና ከአገር ዉጭ ትግሉን አጠናክሮ እንደሚቀጥል፣ ህዝብ ደግሞ የማታ ማታ አሸናፊ እንደሚሆን ሙሉ እምነት እንዳላቸዉ አስረድተዋል።

በጋዜጣዊ መግለጫ ወቅት በርካታ ጥያቄዎች ተነስተዉ በበቂ ሁኔታ ምላሽ የተሰጣቸዉ እንደሆነ ለማወቅ ችለናል። ከተጠየቁት ጥያቄዎች አንዱ ምርጫን የተመለከተ ሲሆን  የአንድነት ፓርቲ በምርጫ የሚያምን ፓርቲ እንደሆነና ለምርጫ እንደሚዘጋጅ ያስረዱት የአመራር አባላቱ ምርጫዉ ዲሞክራሲያዊና ፍትሃዊ ከሆነ እንደሚሳተፉ ገልጸዋል።

አሁን እያየነዉ ያለ አፈናና ወከባ ካልቆመ፣ ነጻና ፍታህዊ ምርጫ ይኖር ዘንድ የሚረዱ ተቋማት ካልተሻሻሉ የአንድነት ፓርቲ የምርጫዉ ተካፋይ እንደማይሆን ከወዲሁ ያስገነዘቡት የአመራር አባላቱ «አንድነት የሚታገለዉ ለኢሕአዴግ የምርጫ አጃቢነት ሚና ለመጫወት አይደለም። ነገር ግን በኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ስርዓት እንዲገነባ እንጂ» ሲሉ ምርጫዉን በተመለከተ አንድነት ያለዉን ቁርጥ ያለ አቋም አስቀምጠዋል።

የአንድነት ፓርቲ ያወጣዉን ሙሉ መግለጫም አያይዘን አቅርበናል።